IPDC
Industrial Parks Development Corporation
የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን

Date ቀን ታሕሣስ 17 2018
Ref.No ቁጥር ኢፓልኮ/003/205/015

# ማስታወቂያ

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ከትላልቅ አምራች ኩባንያዎች የአቅርቦት ሰንሰለት ጋር ማስተሳሰር፣ ፈጠራን ማሳደግ፣ የሥራ ዕድሎችን መፍጠር እና የኢኮኖሚ ዕድገትን ማፋጠን እንዲቻል በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ የማምረቻ ቦታ ለመውሰድ እንዲያመለክቱ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ጥሪ ያደርጋል።

**የመመልመያ መስፈርት፡-**

አመልካቾች የማምረቻ ቦታ ማግኘት እንዲችሉ፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የስታርአፕ/ኢንተርፕራይዝ መመሪያ ቁ.001 መሰረት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

1. ከሚመለከተው የፌዴራል፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ተቆጣጣሪ አካል እውቅና ያለው፣
2. በአግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ ፋርማሲዩቲካልስ፣ ማሽነሪ፣ የሕክምና መሳሪያዎች ወይም ሌሎች ቅድሚያ በሚሰጣቸው ዘርፎች ለኤክስፖርት ወይም ተኪ ምርትን የሚያመርት፣
3. በለማ መሬት ላይ በኮርፖሬሽኑ ስታንዳርድ መሠረት የማምረቻ ሼዱን በራሱ ፋይናንስ መገንባት የሚችል፣
4. ከአገር ውስጥ አምራቾች ግብዓቶችን በመጠቀም፣ ጠንካራ የአገር ውስጥ አቅርቦት ሰንሰለት ትስስር መፍጠር የሚችል፣
5. ለአንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በሥራ ላይ የቆየ እና ለዚህ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
6. ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት (የንግድ እቅድ)፣ የምርት ሞዴልና ስያሜ ማቅረብ እና ለታቀደው ዘርፍ አስፈላጊውን የፋይናንስ አቅም ማሳየት የሚችል፣
7. ኮርፖሬሽኑ ለሥራ ቦታው ያወጣቸውን መመዘኛዎች ስታንዳርዶች ማክበርና መተግበር፣
8. በንግድ ሕግ እንደ ግል ድርጅት ወይም የአክሲዮን ኩባንያ የተመዘገበ፣ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያለው እና ግብር ከፋይ መሆን አለበት እና
9. የሥራ ዕድል መፍጠር እና የእውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማመቻቸት የሚችል።

ማበረታቻዎች እና ጥቅማ ጥቅሞች፡-

የተመለመሉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ከተለያዩ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ በኮርፖሬሽኑ በኩል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

1. በልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ መሰረተ ልማቱ የተሟላ የለማ መሬት ማግኘት፤
2. የአራት ዓመት የመሬት የሊዝ ክፍያ የእፎይታ ጊዜ፤
3. የገበያ ትስስር መፍጠር እና ወደ ትላልቅ የማኑፋክቸሪንግ ደረጃዎች የማሸጋገር ድጋፍ፤

በመሆኑም ፍላጎት ያላቸው አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች አጠቃላይ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎቻቸውን እንዲያዘጋጁ እና ከዚህ ልዩ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይበረታታሉ።

**የማመልከቻ ቦታ፡-**

1. አመልካቾች የፕሮጀክት ፕሮፖዛል እና ደጋፊ ሰነዶችን ቂሊንጦ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን በሚገኘው ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ቢሮ በአንድ ወር ጊዜ (እስከ 19/05/2018 ዓ.ም) በአካል ማስገባት አለባቸው።

+251 118 722313
+251 118 722392
+251 118 722415
www.ipdc.gov.et
Info@ipdc.gov.et
#IPDCEthiopia
#@EthiopiaIpdc
Ipdcofficial
#Ipdcethiopiaofficial
Head quarter
ዋና መስሪያ ቤት